# የቀውስ ማዕከል–እርዳታችን ይፈልጋሉን?

**ቤታችሁ ውስጥ ደህንነት ይሰማችኋልን?**
እንዳለመታደል ሆኖ በየወቅቱ ቤታቸው ውስጥ የጥቃት ተግባር ሰለባ የሆኑ በርካታ ሴቶች፣ ወንዶችና ህጻናት አሉ። ኖርዌይ ውስጥ እንዲህ ዓይነት የጥቃትና የአመጽ ተግባርን 'የቅርብ በሆኑ ሰዎች የሚፈጸም ጥቃት' በማለት እንጠራዋለን። ይህ ማለት ደግሞ ለእናንተ ቅርብ የሆነ ሰው አለ ማለት ነው፤ ለምሳሌ ለጥቃት እንድትጋለጡ የሚያደርጉ የትዳር አጋሮች ማለትም ባል ወይም ሚስት፣ ወላጆች፣ ወንድ፣ እህት ወይም ልጅ ናቸው።

**የጥቃት/የዓመጽ ተግባር ዓይነቶች ብዙ ናቸው:**
- **አካል** (መምታት፣ መጽፋት፣ መጎተት፣ መግፋት)
- **ስነ ልቦናዊ** (ነውረኛ ወይም የብልግና ቃላትን መናገር፣ በነውረኛ ስሞች መጥራት፣ በቁጥጥር ስር ማዋል፣ መነጠል፣ ዛቻና ማስፈራራት)
- **ጾታዊ ወይም ወሲባዊ** (አስገድዶ መድፈር፣ ወሲባዊ የዓመጽ ተግባር)
- **ማቴሪያላዊ** (ቁሳቆችን መወርወር፣ ነገሮችን መሰባበር፣ ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነ ነገርን ማበላሸት)
- **ፋይናንሳዊ** (ገንዘብዎን መቀማት፣ ገንዘብዎን አለመመለስ፣ ያልተረዳችኋቸውን የፋይናንስ ሰነዶችን እንድትፈርሙ ማስገደድ)
- **ያለ ነጻ ፈቃድ የሚፈጸም ጋብቻ** (ሰዎች ከነጻ ፈቃዳቸው ውጭ ጋብቻ እንዲፈጽሙ ማስገደድ/ማስጨነቅ)
- **የሴት ልጅ ግርዛት** (የሴት ልጅ ብልትን መግረዝ)
- **ህገወጥ የሰዎች ዝውውር** (በሴቶች፣ በወንዶችና በህጻናት መነገድ)

**የሆነ ሰው እንዲያነጋግርዎት ይፈልጋሉን?**
በቅርብዎ ከሚገኝ የቀውስ ማዕከል ጋር ይገናኙ። ኖርዌይ ውስጥ ሁሉም ሴቶች፣ ወንዶችና ህጻናት አደጋ ሲያጋጥማቸው ወይም ለጥቃት ሲጋለጡ ከቀውስ ማዕከል እርዳታ የማግኘት መብት አለው።

**ኖርዌይ ውስጥ እንግዳ ነዎትን?**
በቀውስ ማዕከላት የምንሰራ ሰዎች ከሌሎች ሀገራትና ባህሎች የመጡ ብዙ ሰዎች ጋር እንገናኛለን። **ሁሌም አስፈላጊ ሲሆን አስተርጓሚ** እንጠቀማለን። ሰራተኞቻችን ለጥቃት የተጋለጡትን በመርዳት ረገድ ሞያዊ ስልጠና የወሰዱና ልዩ ክህሎት ያላቸው ናቸው። ኖርዌይ ውስጥ ያሏችሁን መብቶች፣ ግዴታዎችና አማራጮችን ያሳውቋችኋል።

ሞያዊ ሚስጥር እንጠብቃለን!ታሪክዎ ከእኛና ከእርስዎ በቀር ለማንም አይገለጥም።እርስዎ ካልፈቀዱና ሊያገኙት የሚሹት እርዳታ ተፈጻሚ እንዲሆን የነገሩንን ሚስጥር ለሚመለከተው አካል መግለጽ የግድና አስፈላጊ መሆኑን እኛና እርስዎ ካልተስማማን በቀር የነገሩን ሚስጥር ሁሉ በምንም ምክንያት ለማንም አንገልጽም።

ሆኖም ህጻናት ተቀባይነት በሌለው የቤት ውስጥ አያያዞችና ሁኔታዎች መሆናቸውን ካወቅን ሁኔታውን ለህጻናት ደህንነት አገልግሎት የማሳወቅ ግዴታ አለብን። በዚህም ህጻናትና ቤተሰቦች ለመልካም ሕይወት የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ ያገኛሉ።

**በሚከተሉት ነገሮች ልንረዳዎት እንችላለን:**
እርስዎና ልጆችዎ ለተወሰነ ጊዜ የሚኖሩበትን አስተማማኝ ቦታ እንሰጥዎታለን ወይም ቤትዎ ውስጥ ለመኖርና ስለሚገኙበት ሁኔታ ለመነጋገር ወደ የቀውስ ማዕከል ለመምጣት ብቻ መምረጥ ይችላሉ። በቀውስ ማዕከል ሀሳብዎን የሚያዳምጥ ባለሙያ ጋር ይገናኛሉ። ከዶክተር፣ ከጠበቃ፣ ከፖሊስ፣ ከኤንኤቪ (NAV)፣ የህጻናት ድጋፍ ድርጅቶች ወይም ሌሎች ኤጀንሲዎች ጋር እንዲገናኙ እንረዳዎታለን።ወደ ስብሰባዎች እንዲሄዱ እንረዳዎታለን ከፈለጉም እንወስድዎታለን። ከማዕከሉ ከወጡ በኋላም እርስዎ ከፈለጉ መገናኘታችንን እንቀጥልበታለን።

ሚናችን ጥቃት ወደሌለበት አዲስና የተሻለ ህይወት በሚያደርጉት ጉዞ የሚያስፈልጋችሁን መረጃ፣ ድጋፍና መመሪያ መስጠት ነው።

AMHARISK